የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ የካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 13
Addis Ababa 12th February, 2007

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፫/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ …… ገጽ ፫ሺ፭፻፳፬

**CONTENTS**

**Proclamation No. 513/2007**

Solid Waste Management Proclamation……. Page 3524

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፫/፲፱፻፺፱

## የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ

ከደረቅ ቆሻሻ የሚከተል አሉታዊ ተፅዕኖን ለመከላከልና ጠቃሚነቱን ለማጎልበት የማኅበረሰቡ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዝቅተኛው የከተማ የአስተዳደር እርከን ታቅዶ የሚተገበር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የድርጊት መርሐ ግብር ማኅበረሰቡን ለማሳተፍ የሚያስችል በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፫/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት" ማለት ባለሥልጣኑ ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ አካል ነው፤

## PROCLAMATION NO. 513/2007.

## SOLD WASTE MANAGEMENT PROCLAMATION

**WHEREAS,** it is essential to promote community participation in order to prevent the adverse effects and to enhance the benefits resulting from solid wastes;

**WHEREAS,** solid waste management action plans designed by, and implemented at, the lowest administrative units of urban administrations can ensure community participation**;**

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation maybe cited as "Solid Waste Management Proclamation No.513 /2007."

### 2. Definition

In this Proclamation:

1/ "Environmental Protection Agency" means the Authority or the environmental protection organ of a Regional State;

፪/ "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፺፭/፲፱፻፺፭ የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

፫/ "ጉድፍ" ማለት የጠርሙስ ስባሪን፣ የብረት፣ የሲጋራ፣ ወይም የወረቀት ቁርጥራጭን፣ የጨርቅ እራፊን፣ የምግብ ትራፊን እና የዕፅዋት ቅሪትን ጨምሮ የተጣለበትን ቦታ ውበት ወይም ንፅሕና የሚያሳጣ የሚጠቅምም ይሁን የማይጠቅም ማንኛውም ነገር ነው፤

፬/ "ሰው ማለት" የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፭/ "ክልል" ማለት በኤትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት በአንቀፅ ፵፯/፩/ የተመለከቱት ክልሎች ማለት ሲሆን በዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲሰ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደርችን ይጨምራል፤

፮/ "ደረቅ ቆሻሻ" ማለት የማይፈለግ ተብሎ የተጣለ ማንኛውም ፈሳሽ ወይም ነፋሽ ያልሆነ ነገር ነው፤

፯/ "የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ" ማለት ደርቅ ቆሻሻን መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ፣ ማከማቸት፣ መልሶ መጠቀም፣ ማስወገድ፣ ወይም አገልግሎት ሰጥቶ ያበቃለትን የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለሌላ ተግባር እንዲውል ማድረግ ነው።

## ፫. የአዋጁ ዓላማ

የአዋጁ ዓላማ ከአያያዙ ሊከተል የሚችል አሉታዊ ተፅዕኖን እየተከላከሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ፋይዳ ከደረቅ ቆሻሻ እንዲገኝ የሚያስችል አቅምን በሁሉም ደረጃ ማጐልበት ነው።

## ክፍል ሁለት
## የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ

## ፬. የከተማ አስተዳደሮች አጠቃላይ ግዴታ

፩/ የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት መስክ ኢንቨስትመንት እንዲ ስፋፋ የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለባቸው።

፪/ ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ፣ በጥቅም ላይ በማዋል ወይም በማስወገድ ተግባር ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው የከተማው አስተዳደር አካል በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

2/ "Authority" means the Environmental Protection Authority established pursuant to Proclamation No. 295/2002;

3/ "Litter" means anything that may or may not have any value, including glass, metal, cigarette butts, paper fabric, food, garden remnants or other materials that in any way spoil the aesthetics of the place or make it unhygienic;

4/ "person" means any natural or juridical person;

5/ "State" means regions states enumerated under Article 47(1) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; for the application of this proclamation State includes Addis Ababa and Diredawa Administrations;

6/ "Solid Waste" means any thing that is neither liquid not gas and is discarded as unwanted;

7/ "Solid Waste Management" means the collection, transportation, storage, recycling or disposal of solid waste, or the subsequent use of a disposal site that is no longer operational.

## 3. Objective of the Proclamation

The objective of this Proclamation is to enhance at all levels capacities to prevent the possible adverse impacts while creating economically and socially beneficial assets out of solid waste.

## PART TWO
## SOLID WASTE MANAGEMENT

## 4. General Obligations of Urban Administrations

1/ Urban administrations shall create enabling conditions to promote investment on the provision of solid waste management services.

2/ Any person shall obtain a permit from the concerned body of an urban administration prior to his engagement in the collection, transportation, use or disposal of solid waste.

## ፭. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ዝግጅት

፩/ የከተማ አስተዳደሮች ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከናቸውንና የአካባቢያቸውን ማኅበረሰብ መነሻ ባደረገ አሳታፊ የአሰራር ዘዴ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲተገበር ማድረግ አለባቸው።

፪/ እያንዳንዱ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ራሱ በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ዘገባ ማዘጋጀት አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተው ዕቅድና ዘገባ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን በሚዘጋጅ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድና በዕቅድ አፈፃፀም ዘገባ ላይ ተመስርቶ መጠናቀር አለበት።

፬/ የከተማ አስተዳደሮች፣

ሀ/ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ የማዘጋጀትና የመተግበር፣

ለ/ ምልክት የተደረገባቸው የጉድፍ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የሕዝብ ማዘውተሪያ ሥፍራዎች መቀመጣቸውን የማረጋገጥ፣

ሐ/ የጉድፍ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻው በየወቅቱ መነሳቱን የማረጋገጥ፣

መ/ የአካባቢ ግንዛቤ ማስፋፊያ ተግባራትን የማቀድና የማከናወን፣

ሠ/ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን የመከላከያ እርምጃ መወሰዱን ማረጋገጥ፣

ኃላፊነቶችን ለዝቅተኛው የአስተዳደር እርከናቸው ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

## ፮. በክልሎች መካከል የሚደረግ የደረቅ ቆሻሻ ዝውውር

፩/ እያንዳንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል በመላክ የሚያስወግደውን ደረቅ ቆሻሻ በተቻለ መጠን ማሳነስ አለበት።

፪/ ክልሎች በክልላቸው አልፎ የሚጓጓዝ ደረቅ ቆሻሻ በሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በወጣ መመሪያና ደረጃ መሠረት ታሽጎ እንዲጓጓዝ ሊያስገድዱ ይችላሉ።

## 5. Solid Waste Management Planning

1/ Urban Administrations shall ensure the participation of the lowest administrative levels and their respective local communities in designing and implementing their respective solid waste management plans.

2/ Each Region or urban administration shall set its own schedule and, based on that, prepare its solid waste management plan and report of implementation.

3/ The plan and report referred to under Sub-Article (2) of this Article shall be consolidated based on the solid waste management plans and implementation reports of the lowest administrative units.

4/ Urban administrations may transfer the following responsibilities to their lowest administrative units:-

a) the formulation and implementation of action plans on solid waste management;

b) ensuring the installation of marked waste bins by streets and in other public places;

c) ensuring the collection of solid wastes from waste bins with sufficient frequency to prevent overflow;

d) planning and carrying out public awareness raising activities;

e) ensuring that measures are taken to prevent pollution arising from the mishandling of solid wastes.

## 6/ Inter-Regional Movement of Solid Wastes

1/ Each Regional State shall keep the shipment of solid waste to other regions for final disposal at the minimum possible.

2/ Regional States may require any transit of solid waste through their region to be packaged and transported in conformity with the directives and standards issued by the concerned environmental agency.

፫/ ደረቅ ቆሻሻን ከአንድ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ወደ ሌላ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ልኮ ማስወገድ የሚቻለው ተረካቢው ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በቆሻሻው መልሶ ለመጠቀም ወይም አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማስወገድ አቅም እንዳለው ለላኪው በፅሁፍ ሲያሳውቅ ብቻ ነው።

## ክፍል ሦስት

## ፯. ጠርሙስና ጣሳ

፩/ የጠርሙስ ወይም የቆርቆሮ ጣሳ አምራች ወይም አስመጪ ጠርሙሱ ወይም የቆርቆሮ ጣሳው የአገልግሎት ዘመኑ እንዳበቃ መልሶ የሚወስድበትን ወይም እንዲወሰድ የሚያስ ደርግበትንና መልሶ በጥቅም ላይ የሚውል በትን ዘዴ መዘርጋትና መተግበር አለበት።

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አተገ ባበር፣ የከተማ አስተዳደሮች ተመላሽ ጠር ሙስ ወይም የቆርቆሮ ጣሳ በጊዜያዊነት የሚከማችበት ቦታ መመደቡንና ክምችቱም በየወቅቱ መነሳቱን ማረጋገጥ አለባቸው።

## ፰. ስለፕላስቲክ ከረጢቶች

፩/ በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ከሚወ ሰነው ቀን ጀምሮ በቀላሉ በስብሶ ወደ አፈር የሚደባለቅ መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ ምልክት ያልተደረገበትን የፕላስቲክ ከረ ጢት ለገበያ ማቅረብ የተከለከለ ነው።

፪/ ውፍረቱ 0.0፫ ሚሊ ሜትር እና ከ0.0፫ ሚሊ ሜትር በታችም ሆኖ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ የፕላስቲክ ከረጢት የማምረት ወይም ወደ ሃገር ውስጥ የማስገባት ፈቃድ መስጠት የተከለከለ ነው።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌ እንደተ ጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ውፍረቱ 0.0፫ ሚሊ ሜትር እና ከ0.0፫ ሚሊ ሜትር የሚያንስ ሆኖ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ የፕላስቲክ ከረጢትን ተለይቶ ለተገለፀ አገልግሎት ብቻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም በአገር ውስጥ እንዲመረት የሚወስን መመሪያ ያወጣል ።

## ፱. የአገለገለ የተሽከርካሪ ጐማ

፩/ የአገለገለ የተሽከርካሪ ጎማን ለማስወገድ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።

3/ Solid waste may be transported from one Regional State or urban administration to another Regional State or urban administration only if the recipient Regional State or urban administration has notified the sender in writing of its capacity to recycle or dispose of it in an environmentally sound manner.

## PART THREE

## 7. Glass Containers and Tin Cans

1/ The manufacturer or importer of glass containers or tin cans shall develop and implement a system that enables it, on its own or through other persons, to collect and recycle used glass containers or tin cans.

2/ For the implementation of Sub-Article (1) of this Article urban administrations shall ensure that pre-collection sites are designated to collect used glass containers and tin cans, and emptied periodically.

## 8. Plastic Bags

1/ As of the date fixed under a directive to be issued by the Authority, it shall be unlawful to put on the market any plastic bag that is not labeled to how whether it is biodegradable or not.

2/ It is prohibited to grant permit for the manufacture or importation of any non-biodegradable plastic bags with a wall thickness of 0.03 millimeters and less than 0.03 millimeters.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the Authority shall, through the issuance of a directive, determine the conditions under which plastic bags with wall thickness of 0.03 millimeters and less than 0.03 millimeters may be imported or manufactured locally for specified purposes.

## 9. Used Tires

1/ The importation of used tires into Ethiopian territory for the purpose of disposal is prohibited.

፪/ የአገለገለ የተሽከርካሪ ጎማ አካባቢያዊ ተቀባይነት ላለው አገልግሎት ወደ አገር ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ፲. ከምግብ ጋር የተያያዙ ደረቅ ቆሻሻዎች

፩/ የምግብ ኢንዳስትሪዎችና የምግብ ቤቶች የሚያመነጩትን ከምግብ ጋር የተያያዘ ደረቅ ቆሻሻ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ መሰብሰብና ማስወገድ አለባቸው።

፪/ ምግብ ቤቶች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓታቸውን የሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ማዘጋጀትና መተግበር አለባቸው።

፫/ ነባር ምግብ ቤቶች የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ የሚመለከት የአካባቢ ኦዲት ማካሄድና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር አለባቸው።

## ፲፩. የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ

፩/ የእያንዳንዱ መኖሪያ ቤት ኃላፊ ለዳግም አገልግሎት የሚውለውን ከናካቴው ከሚጣል ደረቅ ቆሻሻ ለይቶ ለቆሻሻ ማስወገጃ ወደ ተወሰነው ቦታ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

፪/ የከተማ አስተዳደሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አን ቀጽ /፬/ መሠረት በተወሰኑት የመኖሪያ አካባ ቢዎች የመኖሪያ ቤት ደረቅ ቆሻሻ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ በቂ የአገልግሎት መስጪያ መሣሪያዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸ።

፫/ ለዚሁ ተግባር ተብሎ የተዘጋጀ ማጠራቀሚያ በአቅራቢያው እያለ ጉድፍን በመንገድ፣ በጎርፍ መሄጃ ቦይ፣ በፓርክ፣ በአውቶቡስ ወይም በባቡር ጣቢያ፣ በስፖርት ሜዳ፣ በከተማ ውስጥ በሚገኝ የውሃ አካል ወይም በሌላ የሕዝብ መጠቀሚያ ቦታ መጣል የተከለከለ ነው።

፬/ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር የዚህ አን ቀጽ ድንጋጌዎች በግዴታ ተፈጻሚ የሚሆኑ ባቸውን የመኖሪያ አካባቢዎች መከለል አለበት።

## ፲፪. የግንባታና የፍርስራሽ ደረቅ ቆሻሻ

፩/ የከተማ አስተዳደሮች በራሳቸው ወይም ከግን ባታ ድርጅቶች ጋር በመዋዋል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን ወይም የካባ ጉድጓዶችን ከሕንፃ ፍርስራሽ በሚገኝ ጠጠር ወይም አሸዋ ወይም ተቆፍሮ በወጣ አፈር እንዲሞሉ ማድረግ ይችላሉ።

2/ The importation of used tires for environmentally acceptable use shall be determined by directives issued by the Authority.

## 10. Food Related Solid Wastes

1/ Food industries and restaurants shall collect, store and dispose of the food related solid wastes they generate in an environmentally sound manner.

2/ Restaurants shall design and implement solid waste management systems in accordance with directives issued by the concerned environmental agency.

3/ Existing restaurants shall undertake environmental audit and prepare and implement solid waste management plans.

## 11. Management of Household Solid Wastes

1/ The head of each household shall ensure that recyclable solid wastes are segregated from those that are destined for final disposal and are taken to the collection site designated for such wastes.

2/ Urban administrations shall, in the residential areas designated pursuant to Sub-Article (4) of this Article, ensure that adequate household solid waste collection facilities are in place.

3/ It is prohibited to dispose of litter on streets, waterways, parks, bus stops, train stations, sport fields, water bodies in urban areas or in other public places while litter bins are available.

4/ Each urban administration shall delineate residential areas wherein the provisions of this Article shall have compulsory application.

## 12. Construction Debris and Demolition Wastes

1/ Urban administrations may themselves undertake or enter into agreements with construction enterprises to refill solid waste disposal sites or quarry pits with pebbles or gravel from demolished buildings or with excavated earth.

፪/ የግንባታ ፈቃድ የሚሰጠው የግንባታ ፍርስ ራሽ ወይም ተቆፍሮ የወጣ አፈር በተገቢው መንገድ እንደሚያስወግድ የሥራ ተቋራጩ የሥራ አፈፃፀም ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሕጋዊ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ነው።

፫/ ማንኛውም የከተማ መኖርያ ቤት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የከተማ አስተዳደሮች አካባቢያዊ ተቀባይነት ላለው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በቂ ዝግጅት መኖሩን ማረጋገጥ አለባቸው።

## ክፍል አራት

### ፲፫. የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች

፩/ ባለሞተር ተሽከርካሪን ለመመዝገብ፣ ዓመታዊ ምዝገባና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሄድ እንዲሁም የመንጃ ፈቃድ ለመስጠት የሕግ ሥልጣን ያለው አካል ተግባርና ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ወይም መሣ ሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ አገልግሎት የመስጠት ብቃቱ የሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ካወጣው መስፈርት ጋር የሚስ ማማ ስለመሆኑ በከተማ አስተዳደሩ መረጋገጥ አለበት።

፪/ አግባብ ባለው ሕግ የተወሰነው የተሽከርካሪ ክብ ደትና መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር የደርቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ሾፌሮችንና የመሣሪያ አንቀሳቃሾችን ክህሎት ለመወሰን እንዲሁም ከልክ ያለፈ የደረቅ ቆሻሻ ጭነትን ለመከላከል የሚያስፈልጉ መስፈር ቶችን ማውጣት አለበት።

### ፲፬. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ግንባታ

፩/ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር አግባብነት ያለውን የፌዴራል የአካባቢ ደረጃ በመከተል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲገነባና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት።

፪/ የከተማ አስተዳደሮች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ግንባታው በተጀመረ ወይም በተከና ወነ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የአካባቢ ኦዲት መካሄዱን ማረጋገጥ አለባቸው።

፫/ የከተማ አስተዳደሮች አዲስ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሲገነባ ወይም ነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሲሻሻል አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የተካሄደበት መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

2/ Construction permits shall be issued only when the building contractor deposits a legally valid bond or any other instrument to ensure the environmentally sound disposal of construction debris or excavated earth.

3/ Urban administrations shall, before the commencement of any construction of residential houses, ensure the availability of adequate facility for an environmentally sound solid waste management.

## PART FOUR

### 13. Transportation of solid waste

1/ Without prejudice to the mandate of the appropriate agency to register, undertake annual registration and technical inspection of motor vehicles as well as to issue a driving license, the conformity of any vehicle or equipment with the specification set by the concerned environmental agency shall be ascertained by the relevant urban administration prior to its use for solid waste management.

2/ Each urban administration shall, without prejudice to the weight and size of vehicles determined under the relevant law, set standards to determine the skills of drivers and equipment operators and to prevent overloads of solid wastes.

### 14. Construction of Solid Waste Disposal Sites

1/ Each urban administration shall, in conformity with the relevant federal environmental standard, ensure that solid waste disposal sites are constructed and properly used.

2/ Urban administrations shall ensure that a solid waste disposal site that was under construction or was constructed prior to the coming into force of this Proclamation is subjected to environmental auditing as per the relevant law.

3/ Urban administrations shall ensure that any new solid waste disposal site being constructed or an existing solid waste disposal site undergoing any modification has had an environmental impact assessment according to the relevant law.

**፲፭. በነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ላይ የአካባቢ ኦዲት ስለማካሄድ**

፩/ በነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ላይ የአካባቢ ኦዲት መካሄዱን የማረጋገጥ ኃላፊነት የየከተማው አስተዳደር ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በተካሄደው የአካባቢ ኦዲት መሠረት የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃው ቦታ አገልግሎት መስጠት መቀጠል በሕዝብ ጤና ወይም በአካባቢው ላይ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ከተጠ ረጠረ ባለቤቱ አስፈላጊውን ማሻሻያ ማድረግ አለበት።

፫/ ሥራ ያቆመ ወይም የተተወ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ለሌላ አገልግሎት እንዲውል የሚወሰንበትን የአካባቢ መስፈርት ባለሥል ጣኑ በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፮. የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት**

፩/ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከተዘጋ በኋላ በአካባቢ፣ በሰው ጤና ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ ጥፋተኝነት ማረጋገጥ ሳያስፈልግ ባለቤቱ ኃላፊ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከኃላፊነት ነፃ መሆን የሚቻለው ጉዳቱ በተጎጂው በራሱ ወይም ደግሞ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጂያው ባለቤት ኃላፊነት በሌለበት በሦስተኛ ወገን መድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ማንኛውም የካሳ ጥያቄ መቅረብ የሚችለው ጉዳት መድረሱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ውስጥ ይሆናል።

**፲፯. ቅ ጣ ት**

፩/ በሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በወጣ መመሪያ መሠረት ልዩ ፈቃድ ከተገኘ በኋላ እንዲተገበር የተወሰነበትን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ፕሮጀክት ያለፈቃድ የተገበረ ሰው ጥፋት ፈፅሚልና አግባብ ያለው የወንጀል ሕግ ተፈፃሚ ይሆንበታል።

**15. Auditing Existing Solid Waste Disposal Sites**

1/ Each urban administration is responsible for ensuring that an environmental audit is carried out on every existing solid waste disposal site.

2/ The owner of any solid waste disposal site shall make the necessary modifications if the environmental audit made under Sub-Article (1) of this Article shows that its continued operation poses a risk to public health or the environment.

3/ The Authority may prescribe environmental criteria to determine the alternative use of a solid waste disposal site that has ceased operation or is abandoned.

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**16. Civil Liability**

1/ The owner of any solid waste disposal site shall, regardless of fault, be liable for any damage caused to the environment, human health or property in the course of its operation and after its closure.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, exemption from liability shall be granted only when verified that it is the victim himself or a third party for whom the owner of the solid waste disposal sit is not responsible that has caused the damage.

3/ Any claim for damage under Sub-Article (1) of this Article shall be barred by a period of limitation unless brought within two years from the date on which the occurrence of the damage was known.

**17. Penalty**

1/ Without obtaining authorization, a person who implements a solid waste management project that requires special permit before its implementation as determined in a directive issued by the relevant environmental agency commits an offence and shall be liable according to the relevant provision of the Criminal Code.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ መሠረት ፈቃድ መሰጠቱ፣ የፕሮጀክቱን ባለቤት አግባብ ባለው የአካባቢ ደረጃ የተዘረዘረ ተፈላጊ ሁኔታን በመተላለፍ ከሚከተል ሃላፊነት ነፃ አያደርገውም።

፫/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚተላለፍ ማን ኛውም አምራች፣ አስመጪ ወይም ሻጭ ጥፋት ፈፅሞአልና አግባብ ያላቸው የወን ጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ እና /፫/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ስለደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎችን ባለመ ወጣት ጥፋት በሚፈፅም ሰው ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የገንዘብ ቅጣቶችን መወሰንና ማስፈጸም ይችላል።

## ፲፰. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የሚወጡ ደንቦችን በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ The granting of authorization pursuant to the above Sub-Article does not exonerate the proponent from liability that emanates due to contravention of the requirements specified under the relevant environmental standard.

3/ Any manufacturer, importer or seller who violates the provision of this Proclamation commits an offence and shall be liable according to the relevant provisions of the Criminal Code.

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Articles (2) and (3) of this Article, each urban administration may prescribe and enforce fines to be imposed on a person failing to comply with the requirements of this Proclamation relating to solid waste management.

## 18. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives for the proper implementation of this Proclamation and regulations issued under Sub-Article (1) of this Article.

## 19. Effective Date

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of February, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**